# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# የኢየሱስ ተአምራቶች




ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus
ያሻሽለው (አሻሽሎ የጻፈው): E. Frischbutter; Sarah S.
የተተረጎመው: Eyerusalem Dechasa
Alastair Paterson



አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada



©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ኢየሱስ በርካታ ተዓምራቶችን አድርጎ ነበር። ተአምራት ኢየሱስ በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው። የመጀመሪያው ተአምር በአንድ የሠርግ ድግስ ላይ ተከስቶ ነበር። በሰርጉ ላይ ችግር ተከሰተ። ለሁሉም ሰው የሚሆን በቂ ወይን አልነበረም።




የኢየሱስ እናት, ማርያም ስለተፈጠረው ችግር ነገረችው። ከዚያም ለአገልጋዮቹ ኢየሱስ የሚላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ ነገረቻቸው።
3


ኢየሱስም "ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው" አላቸው። "ውሃ?" ብለው ይጠይቁ ይሆናል። አዎን, ኢየሱስ ያዘዘው ውኃ ነው።
4


ኢየሱስም ለአገልጋዮቹ ውሃ ከተሞሉት ከትልቁ ጋን ቀድተው ለባለድግሱ እንዲያቀምሱት አዘዛቸው። ውኃው አሁን ወይን ነበር! ጥሩ ወይን! ምርጥ ወይን!
5


አገልጋዮቹ ተደነቁ። ምክንያቱም ኢየሱስ ውኃውን ወደ ወይን ለውጦታል። እንዲህ ያለውን ተአምራት ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።
6


ኢየሱስ ሌሎች ተዓምራቶችን ማድረግ ጀመረ። በአንድ ምሽት እሱና ደቀመዛሙርቱ ወደ የጴጥሮስ ቤት አቀኑ። የጴጥሮስ አማት በከባድ ትኩሳት ታማ ነበር።
7


ኢየሱስ የታመመችውን ሴት እጅ ዳሰሰ። በዛው ቅፅበት ተፈወሰች። እሷም ኢየሱስንና ደቀ መዛሙርትን ለማገልገል ተነሳች።
8

በዚያም ምሽት የከተማው ሰዎች በበሩ ጋር ተሰበሰቡ። የታመሙ ሰዎችም መጡ - ዓይነ ስውሮች, ደንቆሮዎች, ዲዳዎች, ሽባዎች። በአጋንንት እስራት ውስጥ ያሉ ሰዎችም እንኳ ሳይቀሩ ወደ ኢየሱስ ይጎርፉ ነበር። ይህ ሁሉ ሰው ይረዳ ይሆን?



9

አዎ! ኢየሱስ, የእግዚአብሔር ልጅ ሊረዳቸው ይችላል። ኢየሱስ ረድቷቸውም ነበር። በህይወታቸው ሁሉ በምርኩዝ ሲጓዙ የነበሩ ሰዎች መራመድ ፣ መሮጥ እና መዝለል ቻሉ።



10

ሌሎችም በሥጋ ደዌ የታመሙ ሰዎች መጡ።



11

ኢየሱስም ሲፈውሳቸው ሙሉና ንጹህ ሰዎች ሆኑ።



12

በአጋንንት የተጨነቁ ወንዶች እና ሴቶች በኢየሱስ ፊት ቆሙ። ኢየሱስም ሰይጣኖቹን ከነሱ እንዲወጡ አዘዛቸው። አጋንንቶቹም ሲታዘዙ አስፈሪ እና ደስተኛ ያልሆኑት ሰዎች የተረጋጉ እና ደስተኞች ሆኑ።



13

ከሕዝቡ በስተጀርባ አራት ሰዎች የታመመ ወዳጃቸውን ይዘው ወደ ኢየሱስ መጡ። ነገር ግን ወደ እርሱ መቅረብ አልቻሉም። ምን ያደርጉ ይሆን?



14



የታመመውን ሰውተሸክመው በቤቱ ጣሪያ ላይ ወጡ። አራቱ ታማኝ ጓደኞቹ ጣራውን ቀደው ወደ ታች አወረዱት። አሁን ወደ ኢየሱስ በደንብ ቀረበ።

15

ኢየሱስ እነዚህ አራት ጓደኞች እምነት እንዳላቸው ተመለከተ። የታመመውን ሰው "ኃጢአትህ ተሰረየልህ; መኘታህን አንሳና ሂድ" አለው። ሰውየውጠንካራ ሆኖ ተነሳ። ኢየሱስም ፈወሰው።



16



ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በጀልባ ተሳፍሮ ነበር። ኃይለኛ አውሎ ነፋስ በባሕሩ ላይ ሆነ። ኢየሱስ ግን ተኝቶ ነበር። የተረበሹት ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ከእንቅልፉ ቀሰቀሱት። "ጌታ ሆይ, አድነን መጥፋታችን ነው" ብለው ጮኹ።

17

ኢየሱስም ማዕበሉን "ፀጥ በል!" ብሎ አዘዘው። ወዲያውም ባሕሩ ጸጥ አለ። ደቀመዛሙርቱም "ይሄ ምን ዓይነት ሰው ነው?" ብለው አንሾካሾኩ። ነፋስና ባሕር እንኳን ይታዘዙለታል እነርሱም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብለው አመኑ ምክንያቱም ተዓምራቶቹ ክብሩን ያሳያሉና።



18

የኢየሱስ ተአምራቶች

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ማቴዎስ 8-9፣ ማርቆስ 1-2፣ ማርቆስ 4፣ ሉቃስ 4፣ ሉቃስ 8፣ ዮሐንስ 2

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

19



# መጨረሻ

40

60

20

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16